***የአማራና ቅማንት ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔ***

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 27 የተለያዩ የምርጫ ዓይነቶችን እንደሚያካሂድ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሕዝበ ውሳኔ ነው፡፡ ይህም ሕዝቦች ፍላጎታቸውን ወይም ፍቃዳቸውን የሚገልፁበት አሠራር እና የሕዝብ ፍላጎት በመመልካት አስፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት የሚረዳ እንደሆነ በተሻሻለው የምርጫ ህግ 532/99 አንቀጽ 32 መሠረት ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ጎንደር ዞን በአራት ወረዳዎች የአማራና የቅማንት ሕዝቦች ተቀላቅሎ በሚኖርባቸው 12 ቀበሌዎች ***"በነባሩ አስተዳደር*** ወይም ***በቅማንት ራስ አስተዳደር"*** መተዳደር እንደሚፈልጉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በቁጥር ፌዴም/ምአፈ/5/245 በሐምሌ 13 ቀን 2009 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ ሕዝበ ውሳኔ በማካሄድ የሕዝቡን ፍላጎት በድምፅ እንዲወሰን መጠየቁ ይታወሳል፡፡

በዚህም መሠረት ቦርዱ በጊዜ ሰሌዳ ላይ አስፈላጊውን ግብአቶች በማካተትና በማጽደቅ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

***ሕዝበ ውሳኔ ህግ ማዕቀፍ፡-***

**አንቀጽ 32 - 532/99**

> ፩/ በህገ መንግሥቱ መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የሕዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምፅ የሚስጥበት ስርአት ነው።
>
> ፪/ ሕዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የሚወስነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ቦርዱ ሕዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ሕዝበ ውሳኔውን ያከናውናል።
>
> ፫/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

በዚሁ አዋጅ መሠረት ለሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጪነት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

***በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች፡-***

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ/የሆነች፣
- በአማራ ዞን ስር በሚገኙ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ/የሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች፣
- በቀበሌው 6 ወር የኖረ/የኖረች፣
- የሕዝበ ውሳኔ ተመዝጋቢው በመደበኛነት ነዋሪ መሆኑን እና ማንነቱን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚች/የምትል፣
- አስፈጻሚዎች የተመዝጋቢውን ነዋሪነት ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

***በድምፅ ሰጪነት ሊመዘገቡ የማይችሉ፡-***

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነ/ያልሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ/የሆነች እና በድምፅ መስጫ ጣቢያው ከ6 ወር በታች የኖረ/የኖረች፣
- በአእምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው/የሌላት መሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠበት/የተረጋገጠባት ሰው፣
- የመምረጥ መብቱ/መብቷ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት/የተገደበባት ሰው ናቸው፡፡

*ሕዝበ ውሳኔ ቅድመ ዝግጅት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለሕዝበ ውሰኔው የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን አከናውኗል፡፡

የአማራና ቅማንት ሕዝቦች ተቀላቅሎ በሚኖርባቸው 12 ቀበሌዎች የሕዝበ ውሳኔ በማካሄድ በመረጠው አስተዳደር እንዲተዳደር ለማስቻልና ሕዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ሂደት ለማመቻቸት ቦርዱ የቴክኒክ ኮሚቴ በማዋቀር በቦታው ተገኝተው አጠቃላይ መረጃ እንዲሰበሰብና እንዲደራጅ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በአራቱም ወረዳዎች ለሕዝበ ውሳኔው ተደራሽና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በጎንደር ከተማ ሶስት ምርጫ ጣቢያዎች፣ በጭልጋ ወረዳ 15 (አስራ አምስት) ምርጫ ጣቢያዎች፣ በመተማ ወረዳ 14 (አሰራ አራት) ምርጫ ጣቢያዎች እንዲሁም በቋራ ወረዳ 2 (ሁለት) ምርጫ ጣቢያዎች በድምሩ 34 (ሰላሳ አራት) የምርጫ ጣቢያዎችን አደረጅቷል፡፡ ከምርጫ ጣቢያው ባሻገር ለሕዝበ ውሳኔው ምርጫ ማስፈጸሚያ ከቦታቸው ርቀትና አማካይነት አንጻር ሶስት የወረዳ ማስተባበሪያ ጊዜያዊ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ መሆናቸውን በማመን የጭልጋን ወረዳ የሚያስተባብር በአይከል ከተማ፣ የመተማንና የቋራ ወረዳዎችን የሚያስተባብር በገንዳ ዉሃ ከተማ እንዲሁም የጎንደር ከተማን የሚያስተባብር በጎንደር ከተማ እንዲከፈት አድርጓል፡፡

*ጊዜ ሰሌዳ*

የድምፅ መስጫ ዕለት መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. ሲሆን ከጥዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ የመራጭነት ካርድ የወሰደ መራጭ በሰላማዊ እና በተረጋጋ ሁኔታ ድምፅ መስጠት ይችላል። በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እና የድምፅ አሰጣጥ ገለጻ ለመራጮች የሚሰጠው ነሐሴ 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ነው፡፡

*ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች*

በቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ዝግጅት በቦርዱ ባለሞያዎች የመስክ ጥናት አካሂደው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን መረጃ አደራጅተዋል። በዚህም መሠረት ለሕዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ 34 (ሰላሳ አራት) ምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙ ሲሆን በመተማ ወረዳ አኩሻራ ቀበሌ በለባሳ ምርጫ ጣቢያ በወንዝ ሙላት ምክንያት የምርጫ ጣቢያ ጭማሪ እንዲከፈት ጥያቄ በቀረበው መሠረት ቦርዱ የችግሩን አሳማኝነት በማረጋገጥ በሰጠው አቅጣጫ ገነተ ማሪያም የምርጫ ጣቢያ ከጳጉሜ 3 ቀን 2009 ዓ.ም. ጅምሮ አዲስ የምርጫ ጣቢያ በመክፈት የምዝገባ ሂደቱ ተከናወኗል፡፡ በመጨረሻም የሕዝበ ውሳኔው በአራት ወረዳዎች 8 (ስምንት) ቀበሌዎች 24 (ሃያ አራት) ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የሕዝበ ውሰኔ አካሂዷል፡፡ የሕዝበ ውሳኔው ከሚካሄድባቸው አራት ወረዳዎች ውስጥ፡-

- **በጎንደር ከተማ አስተዳደር** ውስጥ የሚትገኘው ደብረቃ ብላጀግ ቀበሌ ሶስት (3) ምርጫ ጣቢያ ያላት ሲሆን፣ እነዚህም ደብረቃ፣ ጠገድቼ እና አመድጌ የምርጫ ጣቢያዎች ናቸው፡፡
- **በጭልጋ ወረዳ** ውስጥ የሕዝበ ውሳኔው ይካሄዳል ተብሎ የተያዘው በስድስት ቀበሌዎች ውስጥ በ15 (አስራ አምስት) ምርጫ ጣቢያዎች ነው፡፡ እነዚህም ቀበሌዎች ነጋዴ ባህር (2 ምርጫ ጣቢያ)፣ ኳበር ሎምየ (2 ምርጫ ጣቢያ)፣ ናራ አውዳርዳር (5 ምርጫ ጣቢያ)፣ ገለድባ (2 ምርጫ ጣቢያ)፣ አንከር አደዛ (2 ምርጫ ጣቢያ) እና ላዛ ሽምጌ (2 ምርጫ ጣቢያ) ናቸው፡፡
- **በመተማ ወረዳ** ውስጥ የሕዝበ ውሳኔው የተካሄደው በአራት ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ 14 (አስራ አራት) ምርጫ ጣቢያዎች ነው፡፡ እነዚህም ቀበሌዎች ቱመት (5 ምርጫ ጣቢያ)፣ ሸንፋ (4 ምርጫ ጣቢያ)፣ አኩሻራ (3 ምርጫ ጣቢያ) እና ከመቸላ (2 ምርጫ ጣቢያ) ናቸው፡፡
- **በቋራ ወረዳ** ዉስጥ የሕዝበ ውሳኔው የተካሄደው በአንድ ቀበሌ በሁለት ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ነው፡፡ ይህም ቀበሌ ኮዘራ የሚትባል ሲሆን ኮዘራ ሀ እና ኮዘራ ለ በሚባሉ ምርጫ ጣቢያ የተከፈለ ነው፡፡

*የሕዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች*

የሕዝበ ውሳኔውን የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚዎች ከወገንተኝነት ነፃ የሆኑ፣ ሕዝበ ውሳኔ ለማስፈፀም መልካም ስነ ምግባርና የሙያ ብቃት ያላቸው፣ ሕዝበ ውሳኔው ከሚሰጥበት ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ግንኙነት የሌላቸው ከአራት ክልሎች ማለትም ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ብ/ብ እና ሕዝቦች፣ ከቤ/ጉሙዝና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚዎችን መልምሏል፡፡ በተጨማሪም በሕዝበ ውሳኔ አፈጻጸም ዙሪያ ለአስፈጻሚዎች በህግ ማዕቀፍ፣ የምዝገባ ሂደት፣ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እንዲሁም በቅጻቅጾች አተቃቀም የሁለት ቀን ስልጠና በጎንደር ከተማ በመስጠት ወደ ሥራ አሰማርቷል፡፡

*የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች*

ቦርዱ ለሕዝበ ውሳኔው የምዝገባ ሂደትና የድምፅ አሰጣጥ ሂደት የሚያስፈልጉ የሰነድና ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት፣ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በባለ ቀለም ህትመት በማተም በወቅቱ ለምርጫ ጣቢያዎች እንዲደረስ አድርጓል፡፡

*መራጮች ምዝገባ እና የድምፅ ሰጪዎች መረጃ*

ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የመራጮች ምዝገባ የተከናወነው ከነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓ.ም. እስከ መስከረም 3 ቀን 2010 ዓ.ም. ድረስ ቅዳሜ እና እሁድ እንድሁም የበዓል ቀናት ጨምሮ ለአስር ተከታታይ ቀናት ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ እንደተገለጸው የታዛቢዎች ምርጫ የተካሄደባቸው በአራቱም ወረዳዎች 8 (ስምንት) ቀበሌዎች 24 (ሃያ አራት) ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የመራጮች ምዝገባ ሂደት ተከናውኗል፡፡

*የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ*

በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እና የድምፅ አሰጣጥ ገለጻ ለመራጮች የሚሰጠው ነሐሴ 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የሕዝበ ውሳኔው ከሚካሄድባቸው አራት ወረዳዎች ውስጥ፡-

- **በጎንደር ከተማ አስተዳደር** የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ጠገድቼ እና አመድጌ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተከናውኗል፡፡ ደብረቃ ምርጫ ጣቢያ ላይ ግን በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ባይከናወንም ከሕዝቡ ጋር በተደረገው ወይይት ነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓ.ም. ሕዝቡ በምርጫ ጣቢያው በመገኘት ታዛቢዎች እንዲመርጥ ተደርጓል፡፡
- **በጭልጋ ወረዳ** ውስጥ የሕዝበ ውሳኔው ይካሄዳል ተብሎ የተያዘው በስድስት ቀበሌዎች ውስጥ በ15 (አስራ አምስት) ምርጫ ጣቢያዎች ሲሆን፣ ከእነዚህም ምርጫ ጣቢያዎች መካከል በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ የተከናወነው እና የድምፅ አሰጣጥ ገለጻ ለመራጩ ሕዝብ የተሰጠው በሁለት ቀበሌዎች በነጋዴ ባህር እና በኳበር ሎምየ ውስጥ ባሉ አራት ምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ነው፡፡ በቀሩት አራት ቀበሌዎች ናራ አውዳርዳር፣ ገለድባ፣ አንከር አደዛ እና ላዛ ሽምጌ ውስጥ በሕዝቡና መስተዳዳር አካላት ጋር ተጨማሪ የውይይት ጊዜ በመውሰዱ የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ አልተካሄደም፡፡
- **በመተማ ወረዳ** ውስጥ የሕዝበ ውሳኔው በሚካሄድባቸው አራቱም ቀበሌዎች እና አስራ አራቱም ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እና የድምፅ አሰጣጥ ገለጻ ተከናውኗል።
- **በቋራ ወረዳ ውስጥ** በሁለቱም ምርጫ ጣቢያዎች በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እና የድምፅ አሰጣጥ ገለጻ ተከናውኗል፡፡

***የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት አገላለጽ***

***የድምፅ አሰጣጥ ሂደት***

በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጡ ዕለት ከመድረሱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ምርጫ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የድምፅ መስጫ ዕለት መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. በመሆኑ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለመጀመሩ የሕዝበ ውሳኔው አስፈጻሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የነባር አስተዳደርና የቅማንት ራስ አስተዳደር ወኪሎች የመክፈቻ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ከጥዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ የመራጭነት ካርድ የወሰደ መራጭ በሰላማዊ እና በተረጋጋ ሁኔታ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ተጠናቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንደተጠናቀቀ ስለአጠቃላይ ውሎው በዝርዝር ሁሉም አካላት በተገኙበት የድምፅ አሰጣጡ ሂደት መጠናቀቁን የመዝጊያ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ተዘግቷል፡፡

***የድምፅ ቆጠራ***

የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እንደተጠናቀቀ በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች የሕዝበ ውሳኔው አስፈጻሚዎች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የነባር አስተዳደርና የቅማንት ራስ አስተዳደር ወኪሎች በተገኙበት በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት፣ የተበላሹ እና ሥራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣ የድምፅ መስጫ ሳጥኑ እሽግ ያልተከፈተ እና ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ ቃለ ጉባኤ በመያዝ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ተከናውኗል፡፡

የድምፅ ቆጠራ ውጤት እንደተጠናቀቀ በወቅቱ በቦታው የተገኙ የሕዝበ ውሳኔው አስፈጻሚዎች፣ የሕዝበ ታዛቢዎች፣ የነባር አስተዳደርና የቅማንት ራስ አስተዳደር ወኪሎች አጠቃላይ የድምፅ አሰጣጥ እና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም ውጤቱ ትክክል ስለመሆኑ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቃለ ጉባኤ እና የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅጽ ላይ ያለምንም ቅሬታ በመፈራረም ተዘግቷል፡፡ የድምፅ ቆጠራ ውጤት መተማመኛውን ለፈረመው ወኪል አንድ ቅጅ ወዲያውኑ ተሰጥቷል፡፡

***የቆጠራ ውጤት አገላለጽ***

የሕዝበ ውሳኔው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሕዝበ ውሳኔው የድምፅ ቆጠራ ውጤት በድምፅ መስጫ ጣቢያው በይፋ የሚገለፅበት መስከረም 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ነው፡፡ በመሆኑም በሃያ አራቱም የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ውጤት በጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለሕዝቡ ይፋ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አጠቃላይ የሕዝበ ውሳኔው ውጤት ከዚህ በታች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

**የውጤት መግለጫ ዝርዝር**

| ***መረጃው ዓይነት*** | **ቁጥር** | **በመቶኛ** |
|---|---|---|
| የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | *23,283* | |
| ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር | 20,831 | 89.4% |
| ድምፅ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር | 2,454 | 10.5% |
| በጎንደር ከተማ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 3,069 | 13.2% |
| በየጭልጋ ወረዳ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 5,939 | 25.6% |
| በመተማ ወረዳ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 10,866 | 46.7% |
| በቋራ ወረዳ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 3,409 | 14.7% |
| የተሰረዘ ድምፅ | | |
| ዋጋ አልባ ድምፅ መስጫ ወረቀት | 1,744 | 7.5% |

*የሕዝብ ውሳኔውን አስመልክቶ የቀረቡ ቅሬታዎችና የተፈቱበት አግባብ*

*በምዝገባ ሂደት ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችና የተፈቱበት አግባብ*

የአማራና የቅማንት ሕዝቦች ተቀላቀለው በሚኖሩባቸው 8 ቀበሌዎች ውስጥ በተካሄደው የሕዝበ ውሳኔ ወቅት በምዝገባው ሂደት ላይ በአብዛኛው ሰላማዊ ሆኖ ተጠናቋል፡፡ ሆኖም ግን በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የቀረቡት አቤቱታዎች እና የተፈቱበት አግባብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ. ***በጎንደር ከተማ አስተዳዳር***

- በብላጅግ ዳብረታ ቀበሌ በአመድጌ ምርጫ ጣቢያ የአማራ ተወካይ የሆኑት አንድ ግለሰብ መስከረም 5 ቀን 2010 ዓ.ም. የመራጮች መዝገብ ለሕዝቡ ክፍት በሆነበት ወቅት ዕድሜያቸው ያልደረሱ፣ የቀበሌው ነዋሪ ያልሆኑ ተመዝግበዋል የሚል የ36 ሰዎች ዝርዝር ቅሬታ አቅረበው ነበር፡፡ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም ጉዳዩን በመመርመር እና በማስረጃ በማረጋገጥ ያለአግባብ ተመዘገቡ የተባሉት መራጮች ስድስቱ የቀበሌው ነዋሪ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ ሰባቱ በመራጮች መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ መሆናቸው እና የተቀሩት 23 አድራሻቸው የማይታወቅ እና የአባት ስማቸው ያልተገለጸ በመሆኑ ቅሬታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

- በጠገድቼ ምርጫ ጣቢያ የቅማንት ተወካይ የቀበሌ ነዋሪ የሆኑ 100 ሰዎች ከምዝገባ ተከልክለዋል የሚል ቅሬታ ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርበዋል፡፡ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም ቅሬታውን በመመርመር ከምዝገባ ታግደዋል የተባሉት ግለሰቦች የቀበሌ 16 የቁስቋም ጎጥ ነዋሪ መሆናቸውን በማረጋገጥ ቅሬታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለ. ***በጭልጋ ወረዳ***

- በነጋዴ ባህር ቀበሌ ነጋዴ ባህር ሀ ምርጫ ጣቢያ ላይ አንድ ግለሰብ ከመመዝገብ ታግጂያለሁ የሚል ቅሬታ አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ነዋሪ አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ቅሬታውን ወድቅ አድርጓል፡፡

- ነጋዴ ባህር ሀ ምርጫ ጣቢያ ላይ የመራጮች መዝገብ ሊያዩ የመጡ የቅማንት ሕዝቦች ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልደረሱ ሰዎች ላይ እና 55 ሰዎች ላይ ደግሞ 5 ዓመት በቀበሌው አልኖሩም የሚል ቅሬታ አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ተመልክቶ ዕድሜያቸው 18 ዓመት አልሞላቸውም በተባለው ላይ በቤተሰብ (በወላጅ) ዕድሜያቸው መሙላቱ ተመስክሮ እንዲመዘገቡ የወሰነ ሲሆን በ55 ሰዎች ላይ በቀረበው ቅሬታ ሰዎቹ መመዘኛውን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሟሉ እና በሕዝብ ታዛቢዎችና ወኪሎች ተረጋግጦ የተመዘገቡ ስለሆነ ቅሬታው የቀረበባቸው ሰዎች እንዲመዘገቡ ወስኗል፡፡

- ኳቤር ምርጫ ጣቢያ ላይ የእንግድባ ቀበሌ ባርዬ ጎጥ ነዋሪ የሆኑ 43 አባወራ በማሳሳት ተመዝግበው ተገኝተዋል የሚል እና 10 ሰዎች ነዋሪነታቸው የነጋዴ ባህር ቀበሌ ሰለሆነ የምርጫ ካርዳቸው ይመለስ የሚል ከነባሩ አስተዳደር ወኪል በኩል ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ ቀርቦ ነበር፡፡ በማስረጃነትም ከእንግድባ ቀበሌ አስተዳደር እና ከነጋዴ ባህር ቀበሌ አስተዳደር መስከረም 5 ቀን 2010 ዓ.ም. በተፃፈው ደብዳቤ ተረጋግጠው እንዲወጡ የሚል ነበር፡፡ የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም ቅሬታውን ተመልክቶ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተው ነበር፡፡

- የእንገድባው ደብዳቤ ቁጥር ያዘለ አለመሆን፣
- የደብዳቤው መልዕክት ላይ ምርጫ ጣቢያው በፃፈልን መሠረት የሚለው ምንም ዓይነት ደብዳቤ ምርጫ ጣቢያው ለሁለቱም ቀበሌዎች አለመፃፉ እና
- መራጮቹ የተመዘገቡት የሕዝብ ታዛቢዎች ባሉበት ተረጋግጦ በመሆኑ እንዲሁም በየዕለቱ የውሎ ቃለ ጉባኤ በመያዝ የተሠራ ስለሆነ ቅሬታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

- በሌላ በኩል የእንገድባ ቀበሌ ነዋሪዎች ናቸው ተብለው የተዘረዘሩ የ43 ሰዎች ቅሬታ በወረዳ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ቅዳሜ መስከረም 6 ቀን 2010 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ላይ ደርሶ የወረዳው ቅሬታ ሰሚ ከሚቴ በድምፅ መስጫ ቀን መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. በምርጫ ጣቢያው በመገኘት የይግባኝ መዝገቡ በጥንቃቄ መርምሯል፡፡ በምርመራውም አጎራባች እንግድባ ቀበሌ የእኔ ነዋሪዎች ናቸዉ በማለት በስም ከዘረዘራቸዉ 43 ሰዎች ዉስጥ በተራ ቁጥር 1 የተመለከተዉ በምርጫ ጣቢያዉ የሕዝብ ታዛቢ ሆኖ በ402 ድምፅ በዝዝብ የተመረጠ መሆን፤ ምርጫ ጣቢያዉ ሳይጠይቅ በምርጫ ጣቢያዉ ጠያቂነት የተጻፈ ደብዳቤ መጻፉን ጠቅሶ ደብዳቤው ተዓማኒነቱ ያጠራጠረ ቢሆንም አላግባብ ተመዘገቡ የተባሉ 43ቱ ሰዎች የኳቤር ሎሚዬ ቀበሌ ነዋሪነታቸዉ የሚገልጽ መታወቂያ፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ እያቀረቡና በተመሳሳይ ማስረጃ ነዋሪነታቸዉ እየተረጋገጠ ድምፅ እንዲሰጡ እንዲደረግ በማለት ውሳኔ በመስጠቱ ቅሬታው ተፈቷል፡፡ በተጨማሪም የኳቤር ሎምዬ ቀበሌ አስተዳደር ቅሬታ የቀረበባቸውን 43 ሰዎች የኳቤር ቀበሌ ነዋሪዎች ለመሆናቸው መስከረም 7 ቀን 2010 ዓ.ም. ማረጋገጫ በመስጠቱ ይህንን ከሁለቱ ወገኖች ጋር በመተማመንና በመፈራረም ድምፅ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ኳቤር ምርጫ ጣቢያ ላይ 7 ሰዎች በቀበሌው 5 ዓመት አልኖሩም የሚል ቅሬታ አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ተመልክቶ መረጃ ስላልቀረበ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ ተደርጓል።

- ኳቤር ምርጫ ጣቢያ ላይ አንድ ግለሰብ ከመመዝገብ ታግጃያለሁ የሚል ቅሬታ አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ነዋሪነታቸው በምስክር ስለተረጋገጠ እንዲመዘገቡ ወስኗል።

- ሎምዬ ምርጫ ጣቢያ ላይ 3 ሰዎች በቀበሌው 5 ዓመት አልኖሩም የሚል ቅሬታ እና የሌላ ቀበሌ ነዋሪ በመሆናቸው የወሰዱት የመራጮች ካርድ ይመለስ የሚል ቅሬታ የቅማንት ወኪል አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ተመልክቶ መመዝገባቸውን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ***(ይህንን ቅሬታ የወረዳ ምርጫ ፅ/ቤት በይግባኝ አይቶ ሰዎቹ ከምዝገባ እንዲሰረዙ ተደርጓል)***፡፡

- ሎምዬ ምርጫ ጣቢያ ላይ 17 ሰዎች በቀበሌው 5 ዓመት አልኖሩም የሚል ቅሬታ እና የወሰዱት የመራጮች ካርድ ይመለስ የሚል ቅሬታ የቅማንት ወኪል አቅርበው የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ተመልክቶ ምዝገባው በሁለቱ ታዛቢዎች ስምምነት የተከናወነ ስለሆነ ቅሬታውን ወድቅ አድርጓል፡፡ ***(ይህንን ቅሬታ የወረዳ ምርጫ ፅ/ቤት በይግባኝ የምርጫ ጣቢያውን ውሳኔ አጽድቋል)***፡፡

- ነጋዴ ባህር ምርጫ ጣቢያ ለዕድሜያቸው ለመመዝገብ ያልደረሱ መራጭ ተመዝግቧል የሚል እና የመኖሪያው ጊዜው 5 ዓመት ያልሞላው መራጭ ተመዝግቧል የሚል ቅሬታ 30 ሰዎች ላይ ከቅማነት ወኪል ቀርቦ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ቅሬታውን በመመልከት 26 ሰዎች ይመዝገቡ የሚል እና 4 ሰዎች መመዝገብ የለባቸውም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

- ነጋዴ ባህር ምርጫ ጣቢያ ሊ.የቅማነት ወኪል እኛ በሌለንበት የተመዘገቡ መራጮችን ከመዝገብ ቁጥር 1 ከ387 እስከ 496 በመዝገብ ቁጥር 2 ከ384 እስከ 496 ይጣራልን የሚል ቅሬታ አቅርበው የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ መዝገብ ለሕዝብ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ማየት እንደሚችሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ነጋዴ ባህር ምርጫ ጣቢያ ለዕድሜያቸው ለመመዝገብ ያልደረሱ 18 ሰዎች በመራጭነት ተመዝግቧል የሚል ቅሬታ፣ ያለአግባብ የተመዘገቡ 96 ሰዎች እና 29 ሰዎች

ቦርድ ከቅማንት ወኪል ቀርቦ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ቅሬታውን በመመልከት የቀረቡት ቅሬታዎች ህጋዊ ማስረጃ በማህተም የተደገፈ ስላልቀረበ ቅሬታውን ወድቅ አድርጓል፡፡ ***(ይህንን ቅሬታ የወረዳ ምርጫ ፅ/ቤት በይግባኝ የምርጫ ጣቢያውን ውሳኔ አጽድቋል፡፡***)

***ሐ. የመተማ ወረዳ***

- በአኩሻራ ቀበሌ በለባሳ ምርጫ ጣቢያ አንድ ግለሰብ በመራጭነት ከመመዝገብ ታግጃለሁ የሚል ቅሬታ አቅርበው ነበር፡፡ ከሚቴውም የሰው ምስክርነትና የሰነድ ማስረጃ በመመልከት እንዲመዘገቡ ወስኗል።
- በሽንፋ ቀበሌ በሽንፋ ለ ምርጫ ጣቢያ አንድ ግለሰብ አምስት ዓመት ስላልሞላህ በሚል በመራጭነት ከመመዝገብ ታግጃለሁ የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ኮሚቴውም በሶስት የሰው ምስክሮች ነዋሪ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ እንዲመዘገቡ ወሰወኗል፡፡
- በሽንፋ ቀበሌ በሽንፋ ለ ምርጫ ጣቢያ አንድ ግለሰብ አምስት ዓመት ሞልቶኝ እያለ አልሞላህም በሚል በመራጭነት ከመመዝገብ ታግጃለሁ የሚል ቅሬታ ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርበዋል፡፡ ከሚቴውም ቅሬታ አቅራቢው አምስት ነዋሪ ስለመሆኑ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ስላልቻሉ ቅሬታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
- በሽንፋ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያ ሽንፋ ሀ የቅማንት ተወካይ የሆኑ ግለሰብ የመኖሪያው ጊዜው 5 ዓመት ያልሞላው መራጭ ተመዝግቧል የሚል ቅሬታ ቀርቦ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ቅሬታውን በመመልከት ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የቀበሌ ነዋሪነቱን የሚያረጋግጥ ሳይሆን በዚሁ ቀበሌ የዘንባባ መካከለኛ ክልኒክ ተቀጣሪ ሆኖ የተቀጠረበት ውል እንጂ የነዋሪነቱን የሚገልጽ ማስረጃ ባለመሆኑ ቅሬታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

***በድምፅ መስጫ እዕለት ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችና የተፈቱበት አግባብ***

በጭልጋ ወረዳ ኳቤር ሎምየ ኳቤር ምርጫ ጣቢያ ላይ በአማራ ወኪል የ43 ሰዎች ስም ዝርዝር በመጥቀስ ድምፅ እንደይሰጡ የሚል በይግባኝ ለወረዳ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ምርጫ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም በምርጫ ጣቢያው በመገኘት በስም ዝርዝር የተጠቀሱት 43 ግለሰቦች የነዋሪነት ማስረጃ በማቅረብ ድምፅ እንዲሰጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ነዋሪውም የነዋሪነት ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን የኳበር ሎምየ ቀበሌ አስተዳደርም የ43 ግለሰቦች ዝርዝር ቀበሌው ነዋሪ ስለመሆናቸው የማረጋገጫ ሰነድ አቅርቧል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- በጎንደር ከተማ አስተዳደር የደብረቃ ምርጫ ጣቢያ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ አለመከናወን፣
- በቋራ ወረዳ የኮዘራ ቀበሌ የኮዘራ ለ ምርጫ ጣቢያ አዲስ በመሆኑ ቦታ አመራረጥ ተደራሽነት ላይ ያለመግባባት፣
- በመተማ ወረዳ አኩሻራ ቀበሌ በለባሳ ምርጫ ጣቢያ በወንዝ ሙላት ምክንያት የምርጫ ጣቢያ ጭማሪ ጥያቄ፣
- በጭልጋ ወረዳ በአራት ቀበሌዎች ስር ባሉ 11 ምርጫ ጣቢያዎች የምዝገባ ሂደት አለመከናወን፣
- በጭልጋ ወረዳ ኳቤር ሎምየ ቀበሌ ኳበር ምርጫ ጣቢያ ላይ የእንግድባ ቀበሌ ባርዬ ጎጥ ነዋሪ የሆኑ 43 አባወራ በማሳሳት ተመዝግበው ተገኝተዋል የሚል ቅሬታ ቀርቦ የምርጫ ጣቢያውን ውሳኔ ባለመቀበል እና ለወረዳው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅዳሜ መስከረም 6 ቀን 2010 ዓ.ም. ከምሽቱ 12 ሰዓት ያቀረቡ ሲሆን በድምፅ መስጫ ቀን ቅሬታችን ካልተፈታ ድምፅ አሰጣጡ አይጀመርም፣ የሕዝብ ታዛቢዎችም አንፈርምም በማለታቸው የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የወረዳው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቦታው ተገኝቶ ውሳኔ እስከሰጥ ድረስ የድምፅ አሰጣጡ እስከ 2 ሰዓት ልዘገይ ችሏል፡፡

- በዚሁ ምርጫ ጣቢያ በዕለቱ ከቀኑ 8፡30 እስከ ፲፡00 ሰዓት በጣለው ከፍተኛ ዝናብ የደምፅ መስጫ ጣቢያው ድምፅ ማሰጠት ባለመቻሉ በተጠቀሰው ሰዓት ተቋርጦ ነበር፡፡

***የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች***

- በጎንደር ከተማ አስተዳደር የደብረታ ምርጫ ጣቢያ የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ባይከናወንም አስተዳዳሩና ጥምር ኮሚቴው ነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓ.ም. ከሕዝቡ ጋር በተደረገው ወይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መግባባት ላይ በመደረሱ ሕዝቡ በምርጫ ጣቢያው በመገኘት ታዛቢዎች እንዲመርጥ ተደርጓል፡፡
- በቋራ ወረዳ የኮዘራ ቀበሌ የኮዘራ ለ ምርጫ ጣቢያ አዲስ በመሆኑ በአደረጃጃት ተደራሽነት ላይ በአስተዳዳሩ፣ ጥምር ኮሚቴው እና በወረዳው ሕዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ባደረጉት ውይይት አማካይና ለሕዝቡ ተደራሽ በሆኑ ምርጫ ጣቢያዎች በመሄድ መመዝገብ እንዲችሉ በማድረግ ለችግሩ እልባት ተሰጥቷል፡፡
- በመተማ ወረዳ አኩሻራ ቀበሌ የለባሳ ምርጫ ጣቢያ ነዋሪ ሕዝብ በወንዝ ሙላት ምክንያት ለሁለት በመከፈሉ ለሕዝበ ውሳኔው ተደራሽነትና የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ሲባል ተጨማሪ የምርጫ ጣቢያ በገነቴ ማሪያም መንደር ውስጥ እንዲከፈትላቸው የወረዳው ጥምር ኮሚቴ ያቀረበውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ቦርዱ ተጨማሪ ገነተ ማሪያም የምርጫ ጣቢያ በመከፈት የሕዝበ ውሳኔው የምርጫ አስፈጻሚዎችን በመመደብና ሰነድና ቁስቁስ በማዘጋጀት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የምዝገባ ሂደቱ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡
- በጭልጋ ወረዳ በአራት ቀበሌዎች ሥር ባሉ ፲፩ ምርጫ ጣቢያዎች የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫም ሆነ የምዝገባ ሂደት አልተካሄደም፡፡
- በኳቤር ምርጫ ጣቢያ ላይ የእንግድባ ቀበሌ ባርዬ ጎጥ ነዋሪ የሆኑ 43 አባወራ በማሳሳት ተመዝግበው ተገኝተዋል በሚል በቀረበው ቅሬታ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ለሰዓታት የዘገየ ቢሆንም የወረዳው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቦታው በመገኘት ቅሬታ የቀረበባቸው ነዋሪዎች የነዋሪነት ማረጋገጫ ሰነድ እያቀረቡ ድምፅ እንዲሰጡ በወሰነው መሠረት ያለውን ሂደት በቃለ ጉባኤ በመያዝ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ተጀምሯል፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ምርጫ ጣቢያ በእለቱ በጣለው ከፍተኛ ዝናብ የተቋረጠው የደምፅ አሰጣጥ ሂደት የተቀናጀ አሰራር በመፍጠር በተቀመጠው ሰዓት ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡